# “በሃይማኖታዊ ግርዶሽ” ፖለቲካዊ ጥያቄን ማንሳት ይቻላልን?

ያሲን ጡሃ - ከአዲስ አበባ

“ካነበብኩት ነው” በማለት ግሬጅ ዴቪድ የተባሎ ብዕረኛ ሰሞኑን “ህገ-መንግስታዊ ሥርዓታችን ለሃይማኖት ግጭት ቦታ የለውም” በሚል ርዕስ በአይጋ ፎረም ድረ - ገጽ ላይ “እንካችሁ” ያሉን ቅልብጭ ያለና ዕውነታን የሚያመላክት ጽሑፍ፣ እንደ እኔ የበርካታ ሰዎችን ቀልብ ሊስብ የሚችል ነው፡፡ ግና ሃይማኖትና ህገ - መንግስታችን ያላቸውን መስተጋብር የሚገልጸው ይህ ጽሑፍ፣ ቀልብን በመሳብ ብቻ የሚያበቃ አይደለም– ወደ ውስጡ ጎትቶ በማስገባት ከእውነታው ማዕድ እንዲቋደሱና እርስዎም ያለዎትን ሃሳብ እንዲወረውሩ መገፋፋቱ አይቀርምና፡፡… እናም ፀሐፊው ባነሱት ጉዳይ ዙሪያ ጥቂት ሃቆችን ማውሳት ቢያንስ የዜግነት ድርሻን መወጣት በመሆኑ፣ “እኔም ያለኝን እነሆ” በማለት ብዕሬን ከወረቀት ጋር እንዲህ ለማገናኘት ወደድኩ፡፡…

ውድ አንባቢዎቼ እንደምትገነዘቡት፣ በኢፌዴሪ ህገ -መንግስት አንቀጽ 11(3) ላይ “መንግስት በሃይማኖት ጉዳይ ጣልቃ አይገባም፡፡ ሃይማኖትም በመንግስት ጉዳይ ጣልቃ አይገባም” የሚል ጉልህ ድንጋጌ ሰፍሯል፡፡ ይህ ድንጋጌ ሁለት መሰረታዊ ፅንሰ ሃሳቦችን የያዘ ነው፡፡ አንደኛው፣ መንግስት በማንኛውም ሃይማኖት ውስጥ ገብቶ “ይህኛው ትክክል ነው፣ ያኛው ደግሞ የተሳሳተ ነው” የሚል ብያኔ የመስጠት መብት የሌለው ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ ማንኛውም ሃይማኖት በመንግስት አሰራሮች ውስጥ በመግባት “ይህን አድርግ፣ ያንን አታድርግ” በማለት ጣልቃ ገባዊ ተግባርን እንደማያከናውን የሚያመላክት ነው፡፡

ይሁን እንጂ፣ ይህ የመንግስትንና ሃይማኖትን መለያየት በገሃድ የሚገልጸው የሀገራችን ህገ - መንግስት እንደ ማንኛውም ዴሞክራሲያዊ ህገ - መንግስት የዜጎችን የእምነት ነጻነትና የሃይማኖት እኩልነትን የሚፈቅድ ሆኖ ሳለ፣ አንዳንድ የራሳቸውን አጀንዳ ማሳካት የሚሹ ወገኖች ግን ነባራዊ ሃቁን ካለመረዳት ቀደም ሲል ከጠቀስኩት ድንጋጌ ባፈነገጠ መልኩ የተለያዩ የስህተት ሰበዞችን መምዛቸውን ቀጥለዋል፡፡

ምንም እንኳን እነዚህ ወገኖች የእምነትና የሃይማኖት ነጻነት በተከበረበት ሀገር ውስጥ ለምን እንዲህ ዓይነቱን አመለካከት እንደሚያራምዱ ኋላ ላይ የምመለስበት ቢሆንም፣ በህገ - መንግስቱ ማዕቀፍ

ውስጥ እየተንቀሳቀሱ መልሰው ህገ - መንግስቱን ለመጻረር የሚሞክሩት ወገኖች የመንግስትና የሃይማኖት መለያየት እስከየት ድረስ እንደሆነ ማሳየት ተገቢ ይመስለኛል፡፡

አንዳንዴ ሲያሻቸው “የእኛ ሀገር ዴሞክራሲ ሃይማኖትን ልምረጥላቸው ይላል”፤ሌላ ጊዜ ደግሞ “መንግስት እገሌ የሚባል ሃይማኖትን ይደግፋል” ፤ በል ሲላቸውም የህግ የበላይነትን በመጻረር በሃይማኖት መቆራቆስ ሰበብ ልማትን ለማደናቀፍ የሚጥሩት እነዚህ ወገኖች፤ የኢትዮጵያን ልማታዊ ዴሞክራሲያዊ መንግስት ከሃይማኖት አኳያ የሚከተላቸውን መርሆዎች አያውቁም ብሎ ማሰብ አይቻልም፡፡ ግና ነገረ - ስራቸው “አውቆ የተኛን ...” እንዲሉት ዓይነት በመሆኑ፤ መንግስት በሃይማኖት ፣ ሃይማኖትም በመንግስት ”ነጻ ምህዳር” ውስጥ ለምን ጣልቃ እንደማይገቡ መተንተኑን አስፈላጊ ሆኖ አግኝቼዋለሁ፡፡

ማንኛውም የዚህ ጽሑፍ አንባቢ እንደሚያውቀው በየትኛውም ዴሞክራሲያዊ ሀገር ውስጥ የእምነት ነጻነትና የሃይማኖት እኩልነት ያለ ምንም መሸራፈፍ ገቢራዊ መሆናቸው የግድ ነው፡፡ በእኛ ሀገር ውስጥም እነዚህ የሰው ልጅ መብቶች ህገ -መንግስታዊ ዋስትና እና ጥበቃ የተሰጣቸው ጉዳዮች ናቸው፡፡ በመሆኑም አንድ ዜጋ እምነቱን ያለማንም ጣልቃ ገብነት እንዲከተል፤ በሌሎች ዜጎች የአምልኮ አካሂድ ውስጥ ጣልቃ መግባት አይችልም፡፡ ለምን ቢባል፤ ከዴሞክራሲያዊ አሰራር አንጻር የራስን መብት ለማስከበር፣ የሌሎችንም መብት ተመጣጣኝ በሆነ ሁኔታ ሳይጋፉ ማክበር ጥያቄ ውስጥ የሚገባ ጉዳይ ባለመሆኑ ነው፡፡

ታዲያ ይህ እውነታ የሚያስረዳን አንድ ሃቅ መኖሩን መንገንዘብ ያሻል፡፡ ይኸውም የአንድ ግለሰብ የእምነት ነጻነት የሚከበረው የሁሉም ዜጎች አምልኮአዊ የነጻነት ማዕቀፍ ውስጥ መሆኑን ነው፡፡ ይህም የብዙሃኑ መብቶች የሚከበሩት እግረ መንገዱን የግለሰቦችን ተነጻጻሪ መብቶች እውን ያደርጋል፡፡ እናም የሁሉም ዜጎች መብት ሳይሸራረፍ የሚተገበረው፤ ለሀገራችን ዴሞክራሲ መጎልበት ካለው ፋይዳ አኳያ መሆኑን መገንዘብ ያሻል፡፡ እርግጥ እዚህ ላይ ‘የአንድን ሀገር ህዝብ በለተያየ መንገድ የሚያገለግሉት መንግስት ሃይማኖት ምንም ዓይነት ግንኙነት የላቸውም ወይ?‘ የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል፡፡ እውነታውን ግን ወዲህ ነው፡፡...

እንደሚታወቀው ሁለቱ አካላት በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ በራሳቸው አግባብና ነጻነት በመንቀሳቀሳቸው፤ “አይነኬና አይጠጌ” ሆነው መቀጠል የሚችሉ አይደሉም፡፡ ምናልባት ስፋትና ጥልቀቱ የሚለያይ ካልሆነ በስተቀር፤ ሁለቱም ከሀገራቸው ህዝቦች ጋር አብረው የሚሰሩ በመሆናቸው እንደ

ሰሜንና ደቡብ ዋልታዎች የማይገናኙ ናቸው ብሎ መፈረጅ የሚቻል አይመስለኝም፡፡ ምክንያቱም መንግስት ምልዓተ - ህዝቡን በሀገራዊ ሠላም፣ ልማትና ዴሞክራሲ ተግባራት ዙሪያ ለማንቀሳቀስ የመሪነት ሚናውን ሲወጣ፤ የእምነት አስተምህሮቶች ለምዕመናቸው የሚያቀርቡት ሃይማኖቶች ደግሞ ምግባራቸውን ሲከውኑ በአንድም ይሁን በሌላ መንገድ የመገናኘታቸው ምስጢር ሳይታለም የተፈታ በመሆኑ ነው፡፡

ሆኖም መንግስት እያንዳንዱ ዜጋ በህገ - መንግስቱ አማካኝነት ያገኘውን የሃይማኖት ነጻነትን እንደሚያከብር ሁሉ፤ የእምነት እኩልነትም ሳይሸራረፍ ገቢራዊ መሆን እንዳለበት ያምናል፡፡ ከዴሞክራሲ አኳያ በአንድ ሀገር ውስጥ የሚገኙ ዜጎች እኩል በመሆናቸው የሚያከናውኑት ማንኛውም ተግባር ተበላልጦ የሚታይ አይደለም፡፡ በመሆኑም አንድ ግለሰብ የሚያምነው እምነት ከሌላኛው ሊበልጥም፣ ሊያንስም አይችልም፡፡ በሌላ አገላለጽ የትኛውም እምነት ቢሆን የበላይም ሆነ የበታች ሊሆን አይችልም ማለት ነው፡፡ ይህ መሠረታዊ ሃቅ አንድ ግለሰብ ወይም ቡድን በሌላው ላይ የበላይ ለመሆን "እኔ የምከተለውን አምልኮ በግድ ተቀበል" ብሎ ማስገደድ የማይችል መሆኑን ያስገነዝበናል፡፡

መንግስት ባለፉት 20 ዓመታት ባከናወናቸው ተግባራት ቀደም ሲል የጠቀስኳቸውን የእምነት ነጻነትና እኩልነትን በህገ - መንግስቱ አግባብ መሰረት ለማስከበር በርካታ ስራዎችን አከናውኗል፡፡ በተለይም በሃይማኖቶች ውስጥ ጣልቃ ባለመግባት ህገ -መንግስቱን በማክበርና በማስከበር ግዙፍ ክንዋኔዎችን ፈጽሟል፡፡ እርግጥም መንግስት በየትኛውም ሃይማኖት ውስጥ ያሉ ምዕመናን እምነታቸውን በአግባቡ እንዲያከናውኑ ምቹ ሁኔታዎችን ፈጥሯል፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ መንግስት ለየትኛውም ወገን ሳይወግን ይህን ባይከውን ኖሮ፤ ማንኛውም የስራ ኃላፊ ከአመለካከቱና ከእምነቱ በመነሳት በሃይማኖቶች ላይ ተፅዕኖ ማሳረፉ የግድ ነበር፡፡

የትኛውም ሃይማኖት ቀኖናው (doctrine) በሚያዘው መሰረት አምልኮው ሲያከናውን መገናኛ ብዙሃንንን እንዲጠቀም ብሎም የመንግስት የስራ ጊዜ ለበዓላቶቹ ዝግ እንዲሆን በማድረግ የሃይማኖት እኩልነትን ያለምንም ጣልቃ ገብነት እንዲተገበር አድርጓል የኢ.ፌዴሪ መንግስት፡፡ ይህም መንግስት ለማንኛውም እምነት ምቹ የማምለኪያ መደላድል ከመፍጠርና ሚዳውን በእኩልነት መንፈስ ማመቻቸቱን የሚያመላክት እውነታ ነው፡፡ ሆኖም ቀደም ሲል የጠቀስኳቸውና "ታመመ" ሲባል "ሞተ" ማለት የሚቀናቸው አንዳንድ የራሳቸውን ህቡዕ ዓላማ ለማራመድ የሚሹ ወገኖች በ"ቆርጦ ቀጥልነት" "የእኛ

ሀገር ዴሞክራሲ ሃይማኖታችሁን ልምርጥላችሁ ይላል" እያሉ እንደሚያስወሩት ሳይሆን፤ ሃቁ መንግስት ለዴሞክራሲያችንን ማበብ ካለው ጽኑ እምነት በየትኛውም ሁኔታ፤ በሃይማኖት ውስጥ ጣልቃ ገብቶ የማያውቅ መሆኑ ነው፡፡

ይህ ማለት ግን ሃይማኖቶች በአንድ ሀገር ውስጥ በተሳሳተ መንገድ ሲንቀሳቀሱ መንግስት "እኔና እነርሱ ስለተለያየን፣ ጉዳዩ አይመለከትኝም" በማለት እጁን አጣጥፎ ይቀመጣል ማለት አይደለም፡፡ ለምን ቢባል፤ መንግስት ህዝቦቹን በሠላም፣ በልማትና በዴሞክራሲ ዙሪያ በማሰባሰብ ሀገራዊ ለውጥ ለማምጣት የመሪነት ሚናውን ሲወጣ፤ ሃይማኖቶች ደግሞ ከምዕመናቸው ጋር የእምነት ተግባራቸውን ሲያከናውኑ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ የመናገኘታቸው ምስጢር ሳይታለም የተፈታ ጉዳይ በመሆኑ ነው፡፡ እርግጥም የሚመራቸውን ህዝቦች አሰባስቦና ከዳር እስ ዳር አነቃንቆ በምድር ላይ እስካሉ ድረስ ተጠቃሚ እንዲሆኑ የሚሰራው መንግስት፤ ለተመሳሳይ ዜጎች "ሰማያዊ" ክንዋኔዎችን ከሚተገብሩት ሃይማኖቶች ጋር መገናኘቱ አይቀሬ ነው፡፡

ምንም እንኳን ሃይማኖቶች "ሰማያዊ" ዕድትን ለምዕመናኑ ለማስገኘት የሚሰሩ ቢሆንም፤ ተግባሩን ተፈጻሚ የሚያደርጉት በምድር ላይ እና በመንግስት ማዕቀፍ ውስጥ ስለሆነ መገናኘታቸው የግድ ነው፡፡ ታዲያ እዚህ ላይ ሁለቱ አካላት የማይገናኙት አንደኛው ተገቢ ባልሆነና በህግ ከተደነገገው ውጭ በሌላኛው አሰራሮች ውስጥ ጣልቃ እስካልገባ ድረስ ብቻ መሆኑን ውድ አንባቢዎቼ እንደምትገነዘቡልኝ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡ መንግስት ለልማት ሲተጋ፣ ሃይማኖቶች ከዚህ እሳቤ በተጻራሪ ቆመው ተግባሩን ለማደናቀፍ ጥረት ካደረጉ፤ እርግጥም "የመለያየ ወሰኑን" ጥሰው አልፈዋልና "ጣልቃ ገብነቱን" ለማስቆም የማስተማር እርምጃዎችን መውሰዱ አይቀሬ ነው፡፡ ምክንያቱም መንግስት የህዝቦቹን መሰረታዊ ዴሞክራሲያዊ መብቶችን የማስከበር ግዴታና ኃላፊነት ያለበት በመሆኑ ነው፡፡

እንደሚታወቀው በሀገራችን ውስጥ ያሉት ሁሉም ሃይማኖቶች ሰላምን፣ ፍቅርን፣ መቻቻልን የሚያስተምሩ እንጂ፤ የግጭትና የብጥብጥ አስተምህሮት መነሻ ያላቸው አይደሉም፡፡ በመሆኑም የመንግስት ተግባራትን ለማደናቀፍ ስራዬ ብለው የሚንቀሳቀሱበት አንዳችም መመሪያ በውስጣቸው የለም። እናም ፀረ - ዴሞክራሲያዊነትን ሊያራምዱ የሚያስችላቸው አቋም ሊኖራቸው አይችልም፡፡ ይሁን እንጂ፤ በየሃይማኖቱ መካከል የሚገኙ ጥቂት የራሳቸውን የፖለቲካ አጀንዳ ማራመድ የሚሹ ወገኖች

የሃይማኖቶችን ተከታዮች "ጠንካራ" እና "ለዘብተኛ " እያሉ በመከፋፈል ድብቅ ዓላማቸውን ለማሳካት ምዕመናኑን ለማሻኮት ጥረት ያደርጋሉ፡፡

እነዚህ ወገኖች ሃይማኖትን እንደ መሸሸጊያ ዋሻ በመጠቀም "እገሌ የሚባል አስተምህሮት ብቸኛው ስለሆነ እርሱን ተከተል" በማለት የእኩልነት መርህን የመሳሰሉ መሠረታዊ የዴሞክራሲ መርሆዎችን ሆን ብለው ይጥሳሉ፡፡ በዚህ ፀረ - ህገ -መንግስት እሳቤያቸውም ጠንካራ አማኞች በመምሰል፣ በየሃይማኖቶቹ ውስጥ የአክራሪነት ስሜት እንዲፈጠር የማይፈነቅሉት ድንጋይ አለ ማለት አይቻልም፡፡

ታዲያ እንዲህ ዓይነቱ የአክራሪነት አመለካከት ፖለቲካዊ ይዘት ያለው ከመሆኑም ባሻገር፣ ከጥቂት ጊዜ በኋላ በአብዛኛዎቹ እምነቶች ውስጥ በጣት በሚቆጠሩ ግለሰቦች አማካኝነት መራገብ ከጀመረ ሰነባብቷል፡፡ በኦርቶዶክስ፣ በእስልምናም ይሁን በሌሎች ሃይማኖቶች ውስጥ ይህን መሰሉ ክስተት ብቅ ጥልም እያለ መታየቱ የዚሁ ነጸብራቅ ይመስለኛል፡፡ እስቲ እዚህ ላይ ለውድ አንባቢዎቼ ግንዛቤ ይረዳ ዘንድ፣ በኦርቶዶክስና በእስልምና እምነቶች ውስጥ ሊፈጠሩ የሚችሉና በፀረ - ህገ - መንግስታዊ አስተሳሰብ ሳቢያ የተጀመረውን ፈጣንና ተከታታይ ዕድገት የሚገቱ የተሳሳቱ የአክራሪነት አካሄዶችን ለመጥቀስ ልሞክር፡፡

ቁጥራቸው እጅግ አናሳ የሆኑ የኦርቶዶክስ ሃይማኖት ተከታዮች በየእምነት ተቋማቱ ውስጥ የራሳቸውን ድብቅ ፖለቲካዊ ዓላማ ለማካሄድ ሲያሻቸው "አንድ ሃይማኖት፣ አንድ ሀገር" ፤ሌላ ጊዜ ደግሞ የተለያዩ አመለካከቶች ያሏቸውን ክርስቲያኖችን በማውገዝ የአምልኮ ሥርዓታቸውን እንዳያከናውኑ እንቅፋት ይፈጥራሉ፡፡ በዚህም አላስፈላጊ ብጥብጥ እንዲፈጠር ተግተው ይሰራሉ፡፡ በእስልምናም እምነት ቢሆን ከዚህ የተለየ ሁኔታ አይስተዋልም፡፡ ጥቂት በሃይማኖቱ ስም የተደራጁ ወገኖች፣ ሌላውን የእምነቱ ተከታይ ዜጋን፣ "ሃቀኛ ሙስሊም አይደለም" የሚል ስያሜ በመስጠት የራሳቸውን- ፖለቲካዊ ይዘት ያለውን ቀኖና በኃይል ለመጫን ይፈልጋሉ፡፡ ይህ ብቻም አይደለም– "ሃይማኖታችን መስፋፋት አለበት" በሚል ሽፋን የራሳቸውን ፖለቲካዊ እሳቤ በመንግስትና በተቋማቱ ውስጥ ተፈጻሚ ለማድረግ የሚሹ ወገኖችም መኖራቸው አይቀርም፡፡

እርግጥም መንግስት እንዲህ ዓይነቶቹን የለየላቸው ፀረ - ህገ-መንግስታዊ አመላከቶች፣ የሃይማኖትና የእምነት ነጻነት በተከበረበት ሀገር ውስጥ ሲንሸራሸሩ ዝም ብሎ መመልከት ያለበት አይመስለኝም፡፡ አዎ! መንግስትም በማከናወን ላይ የሚገኘው ይህንኑ ተግባር ነው፡፡ የትኛውም ሃይማኖት የዜጎችን መሠረታዊ

መብት በመርገጥ አሊያም መንግስትና ሃይማኖት የሚለያዩበትን ገመድ በመበጠስ ከተንቀሳቀሰ፤ በፀረ - ዴሞክራሲያዊነት መፈረጃቸው የግድ ይሆናል፡፡ በተግባራቸውም ዜጎች ለሀገራቸውና ለራሳቸው ዕድገት በልማታዊ ስራ ከመሳተፍ ይልቅ፤ ጊዜያቸውን በእምነት ሳቢያ በሚፈጠሩ ንትርኮችና ብጥብጦች እንዲያባክኑ የሚያደርጉ ከሆነ፣ መንግስት ሁለት ዓይነት ተግባራትን መከወኑ አይቀሬ ነው፡፡

የመጀመሪያው እና ቀዳሚው  አሁን እያደረገ እንዳለው ተግባሩ ፀረ - ህገ መንግስታዊ መሆኑን የማስተማርና የማሳወቅ ስራዎችን ማከናወን  ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ ህግና ስርዓትን የማስከበር ኃላፊነትና ግዴታ ስላለበት አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የማስተካከያ እርምጃዎችን ሊወስድ ይችላል፡፡ ታዲያ እዚህ ላይ መሰመር ያለበት ትልቅ ቁም ነገር፤ አንዳንድ የራሳቸው የፖለቲካ አጀንዳ ያላቸው ወገኖች “መንግስት እገሌ የሚባል እምነትን ይደግፋል” እያሉ እንደሚደሰኩሩት ሳይሆን፤ በአሁኑ ወቅት እየፈጸመ ያለው በእስልምና ሃይማኖት  ውስጥ በማቆጥቆጥ ላይ የሚገኙ ፀረ - ዴሞክራሲያዊ አስተሳሰቦችን የማረቅ ተግባር ነው፡፡ ይህ የማስተማርና የማሳወቅ እንቅስቃሴው መንግስታዊ ግዴታው እንጂ፤ ሁሌም በመንደር አሉባልታ የሚዋትቱ አንዳንድ ወገኖች እንደሚያስወሩት አንዱን በመደገፍና ሌላውን በመንቀፍ አለመሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

ይሁን እንጂ፤ የከሰሩ ፖለቲከኞች  የፖለቲካው ምህዳር አንጓሎ ሲጥላቸው ሃይማኖት ውስጥ ተወሽቀው መንግስትን ለማብጠልጠል መሞከራቸውና የህዝቡን ልማታዊ ዕድገት በጭቅጭቅ  የኋሊት ለመጎተት መጣራቸው ሊወገዝ የሚገባው ተግባር ነው፡፡ ማንኛውም  ግለሰብ፣ ቡድን ወይም ሃይማኖት ተግባሩን ማከናወን የሚችለው በህገ - መንግስቱ ጥላ ስር ሆኖ  ሳለ፤ እነዚህ ወገኖች  ህግና ሥርዓትን ተጻርረው “የእኛ እምነት ብቻ ትክክል ነው” በሚል ፀረ - ዴሞክራሲያዊ እሳቤ ከተንቀሳቀሱ፤ መንግስት ተግባራቸው ፖለቲካዊ  እንጂ ሃይማኖታዊ አለመሆኑን ስለሚገነዘብ ዴሞክራሲያዊ አስተምህሮትን መከተሉ ሊያስመሰግነው የሚገባ መሆኑ አሌ አይባልም፡፡

አዎ! አንድ ቡድን “የፖለቲካ ዓላማዬን  አሳካለሁ” ብሎ ካሰበ፤ ተግባሩን  መከወን ያለበት በቤተ - እምነቶች ውስጥ አይደለም–ራሱን በፖለቲካ ፓርቲነት በማደራጀት እንጂ፡፡  በመሆኑም ቡድኑ በፖለቲካ ፓርቲነት መደራጀቱ እንደማያዋጣው ስለተገነዘበ ብቻ፤ ሃይማኖትን እንደ መከላከያ ምሽግ በመቁጠር የእምነቱን ተከታዮች ሊያምሳቸው አይገባም፡፡ ለአብነት ያህል የእስልምና እምነትን የሚከተሉ አንዳንድ ወገኖች “በሸሪዓ መተዳደር አለብን” በሚል  የሚያነሱትን ጥያቄ መመልከት ከዚህ አኳያ መመልከት

ይቻላል። ታዲያ ይህን ጥያቄያቸውን በየዋህነት ላይ ላዩን ለሚመለከተው ህዝብ ሃይማኖታዊ ሊመስል ይችላል፡፡ እውነታው ግን ይህ አይደለም፡፡ ከሀገራችን አኳያም “መንግስትና ሃይማኖት ተለያይተዋል” የሚለውን ህገ - መንግስታዊ ድንጋጌ የሚጻረር፣ ዓላማው ሃይማኖታዊ መንግስት እንዲፈጠር የሚሻ ተግባር ነው፡፡

እርግጥም እንዲህ ዓይነቱ “በሸሪዓ እንተዳደር ቡድናዊ ጥያቄ” ከእስልምና አስተምህሮት ጋርም የሚጋጭ ነው፡፡ ነብዩ መሃመድ (ሰ.ዐ.ወ) ደጋግመው እንዳስተማሩት፣ ኢስላም በግሉ የጽድቅ መንገድን መከተል እንዳለበት ነው፡፡ ይህም ማንኛውም አማኝ በግሉ አምኖ በግሉ እንደሚጸድቅ የሚያመላክት መሆኑ ሲነገር የኖረ ጉዳይ ነው፡፡ ስለሆነም “በሸሪዓ መተዳደር” በእስልምና እምነት የግድ አለመሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡

ታዲያ እዚህ ላይ ‘እነዚህ በሃይማኖት ጭንብል ተሸፍነው፣ የሚንቀሳቀሱት ወገኖች እነማን ናቸው?’ የሚል ጥያቄ ማንሳት ተገቢነቱ አያጠያይቅም፡፡ እርግጥም እነዚህ ጥቂት ቡድኖች ከሃይማኖት መመሪያዎች ውጭ በመሆንና አክራሪነትን እንደ “ስራ ማስኬጃ” ካርድ የሚጠቀሙ ፀረ - ህገ - መንግስት ባለሚሎች ናቸው ብል ማጋነን አይሆንብኝም፡፡ ምክንያቱም ሃይማኖታዊ እምነቶችን ወደ ጎን በመግፋት ዜጎች እንዲበጣበጡ ብሎም ትኩታቸውን በጀመሩት ልማታዊ ስራዎች ላየ እንዳያደርጉ የሚሹ ኃይሎች በመሆናቸው ነው፡፡ እንደ እኔ እምነት፣ እነዚህ ወገኖች ሃይማኖትን በመጋረጃ ግርዶሽነት የሚጠቀሙና በአንድም ይሁን በሌላ መልኩ ኪሳራ የደረሰባቸው ፖለቲከኞች አሊያም በእነርሱ ፈረስ ላይ ተፈናጠው ሽምጥ ለመጋለብ የሚዳዳቸው ኃይሎች ነው፡፡ ዓላማቸውም የሌሎችን ዴሞክራሲያዊ መብት በመደፍጠጥ በአቋራጭ የስልጣን እርካብ ላይ መንጠላጠል መሆኑ የሚታበይ አይመስለኝም፡፡

ዳሩ ግን ‘በሃይማኖታዊ ግርዶሽ ፖለቲካዊ ጥያቄን ማንሳት ይቻላልን?’ የሚል ጥያቄን ብናነሳ፣ ምላሹ በመግቢያዬ ላይ የጠቀስኳቸው የብዕር ሰው እንዳሉት የሀገራችን ህገ - መንግስታዊ ሥርዓት ለሃይማኖት ግጭት ቦታ የለውም የሚል ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ አዎ! ዴሞክራሲያዊው ሥርዓት ፀረ - ዴሞክራሲያዊ እሳቤዎችን የሚሸከምበት ጫንቃ የለውም፡፡ መንግስትም ከተፈጥሮአዊውና ይዞት ከመጣው ዴሞክራሲያዊ ባህሪው ባፈነገጠ መልኩ የትኛውንም የሃይማኖት አስተምህሮት አይደግፍም፣ አይቃወምም፡፡ ዋነኛ ተግባሩ ሃይማኖቶች ከመንግስት ጋር የተለያዩበትን ገመድ ለመበጠስ ሲሞክሩ ማስተማርና ማሳወቅ

ነው፡፡ ሃይማኖትን እንደ መጋረጃ ጋርደው ፖለቲካዊ ጥያቄ ያላቸውን አክራሪዎችንም ቢሆን ከዚህ ውጪ የሚመለከታቸው አይመስለኝም፡፡

ይሁንና እኔን ጨምሮ ማንኛውም የዚህ ጽሑፍ አንባቢ እንደ ዜጋ፤ የግልና የቡድን ዴሞክራሲያዊ መብቶቻችን እንዲረገጡ፣ በሠላም ወጥተን የምንገባበት ሁኔታዎች እንዳይኖሩ እና ልማታዊ ተጠቃሚነታችን እንዲቀሩ የምንፈልግ አይመስለኝም፡፡ በመሆኑም እነዚህ ድርጊቶች እንዳይፈጸሙ፣ የመቻቻል ባህላችንን ተመርኩዘን ሃይማኖቶች ውስጥ ተሸሽገው እክራሪነትን የሚቀምሩ ኃይሎችን ማውገዝ ይኖርብናል፡፡

ለዚህም ሁላችንም በየእምነታችን ውስጥ ከሚራመዱ የአክራሪነት አስተሳሰቦች ፖለቲካዊ ይዘት ጀርባ ማን እንዳለ በትክክል በመመርመር የግራና ቀኙን ምልከታዎች በአግባቡ ማጤን ይጠበቅብናል፡፡ ስለሆነም እያንዳንዳችን ‘የምከተለው ሃይማኖት ከአክራሪ ፖለቲከኞች አመለካከት ምን ያህል የጸዳ ነው?፣ ሃይማኖቴስ ለፀረ - ህገ - መንግስት ኃይሎች በዋሻነት እያገለገለ ነውን?’ የሚሉና ሌሎች ሰላማዊ ጥያቄዎችን አንስተን "ሃይማኖታዊ ግርዶሽን" የሚጠቀም ፖለቲካዊ ፍላጎትን ማራመድ እንደማይቻል ማሳየት የሁላችንም ድርሻ መሆን አለበት፡፡ ቸር እንሰንብት።